ግንቦት 30 1997ዓ ም

# <u>መልዕክተ ኢሕአፓ</u>

ይድረስ ለተማሪዎችና ወጣቶች
ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ

ትላንትም ቢሆን ውድ ሀገራችንን ከጭንቀቷና ከወራሪዎች የገላገላት ሕዝቧ ነውና ሊያጠፉት በመጣው የወያኔ ቡድን ላይም አምርሮ በመነሳት ዛሬም ሊያድናት እየጣረ ያለው ሕዝቧ ነው:: ትላንት ላስተማራቸው ሕዝብ መብትና ለሀገር ልዕልና ታሪክ የማይረሳው ትግል ያካሄዱና መስዋዕትነትንም የተቀበሉ የሀገሪቷ ወጣቶችና ተማሪዎች ነበሩና ዛሬም የሕዝብ ድምፅ አይሰረቅም ብለው ሊታገሉ የተነሱት ወጣቶችና ተማሪዎች ታሪክ አለመዋሸቱን፤የትግል መንፈስና ሀገር ወዳድነት አለመክሰሙን ያበስራሉ:: ኢሕአፓ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የጀመሩትን ትግል ሙሉ በሙሉ ይደግፋል:: የዋጣቶች ትግልና ቆራጥነት የወለደው ድርጅት ነውና ታመሪውና ወጣቱ ለሀገር ብሎ ሲነሳና ሲያምፅ ኢሕአፓ እሰየው ብሎ ከጎናቸው ይቆማል እንጂ፥ ምን ቢመጣ ምን ሽብረክ-ሽርተት አይልም:: የወጣቱ ትግል ደግሞ፥ ወላጆችንና ሰፊውንም ሕዝብ የሚነካ ነውና ኢሕአፓ በርቱ ጠንክሩ የሚለውን ጥሪ ሲያሰማ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ትግል እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ባለው አቅሙ እየጣረ ነው::

ተማሪዎች ሲታገሉ ብቻቸውን ከሆነ ለአረመኔው ሥርዓት ጥቃት ይጋለጣሉና በየካቲት 66 እንደታየው ሁሉ ሌላውም የህብረተ ሰቡ ክፍል አብሯቸው ሊነሳና ሊያምፅ ይገባል:: ተቃዋሚ ድርጅቶች ይህንን ትግል ማፋፋምና ማጠናከር ተቀዳሚ ግዳጃቸው መሆኑንም ማወቅ አለባቸው:: ሰፊው ሕዝብም ማለትም ሠራተኛው፤አርሶ አደሩ፤ የቢሮ ሠራተኛው፤ ሴት ወንዱ፤ ካህን ሼኩ፤ ወታደሩና ፖሊሱ ክፍልም ቢሆን፥ ከዚሁ የመብት አስከባሪ ሀገራዊና ሰላማዊ ትግል ጎን መቆም አለበት:: ግብታዊነትን በድርጅትና ሰልት ባለው መንገድ ለመተካት ደግሞ፥ ድርጅቶች ደፈር ብለው በመሪነት መሰየምና ትግሉን መምራት፤መስዋዕትነቱንም መቀበል ይኖርባቸዋል:: ሩቅ ሳንሄድ የየካቲት 66 ተመክሮ ይህንን ያሳይቶናል፤አስተምሮናል:: ማንኛውም ተቃውሞ የሚገጥመው አምባገናናዊ አገዛዝ፥ ሕዝብን ማስፈራራትና የአፈና እርምጃ መውሰድ የመጀመሪያ ምርጫው ነው:: የሕዝብን የምርጫ ድምፅ የሰረቀው ወያኔም ሌላ ጠባይ ሊያሳይ አይጠበቅም:: ታዛዥ ጦሩን አሰማርቶና ተቃውሞና በወንጀል ፈርጆ ሊያፍን ሊገድል ይጥራል:: የተቃዋሚዎችን ወኔ ይፈትናል:: ፅናታቸውን ይለካል:: ይህ ያለና የነበረ የሚጠበቅም ነው:: ለዚህም ነው ለአገዛዙ ጊዜ መስጠት ሳይሆን፤ መለሳለስ ሳይሆን፤ የለንበትም ሳይሆን፤ አደብ ግዙ ብሎ ጩኸት ሳይሆን፥ አገዛዙ ይወገድ ብሎ ትግልን ማፋፋም ነው

የሚገባው:: በሕዝብ የተጀመረው፤በተማሪዎች የተቀጣጠለው ሰደድ እሳት ሆኖ ህግ ወጡን ቡድን ከሥልጣን እንዲያስወገድ መሟሟት ያስፈልጋል::

ለዚህም መሠረቱ ህብረት ነው:: የተቃዋሚዎች ህብረት፥ በመጀመሪያ የተናጠልን ትግል በጋራ ትግል ማጀቡም መሠረታዊ ነው:: አገዛዙ በተማሪዎች ላይ እርምጃ ሲወስድ ዝም ብሎ አለማየት:: በጋራ ማመፅ፤ መነሳትና መታገል የግድ ይሆናል ማለት ነው:: አገዛዙ የሚያውጅውን ማክበር ሳይሆን፥ መጣስ፤ አልቀበልም ማለት፥ አልገዛም ማለት ተገቢ ነው:: መብታችን ነው ማለትም ነው:: በዚህ ወሳኝ ወቅትም ፈሪ ተለይ ማለቱም የግድ ይሆናል:: ከህዝብ ጎራ ነኝ እያለ ግን የሚርበተበተውና በቃ እናብቃ የሚለውን ማራቅ ያስፈልጋል:: በፅናት ጊዜ ፍርሀትን የሚሰብኩ፤ ትግሉ ገና ሲጀመር እጅ መስጠትን የሚሰብኩ ከሕዝቡ ጎራ መሆን የለባቸውም:: ሞተው የሚያሞቱ ትግልን ያደናቅፋሉ እንጂ አያጠናክሩትምና ነው:: የመለስ ቡድን ሰላማዊ ተቃውሞን የከለከለው ህገ ወጥ እርምጃው የሕዝብን ቁጣና እምቢታ እንደሚያስከትል በማወቁ ነው:: ሕዝብ ግን ይህንን ህገ-ወጥ እርምጃ ሊያከብር የሚጠበቅ አይደለም:: በስልት በልዩ ልዩ መንገድ ተቃውሞውን መፋፋም አለበት:: በተናጠል ሳይሆን በጋራ:: ለአንዴ ሳይሆን ሳያቋርጥ እስከ ድል:: ሥርዓቱን ስንታገል ደግሞ በሌላ በኩል አገዛዙ ለመነጠል በስልት መሞከር ተገቢ ይሆናል:: የትግራይ ተወላጆች በአገዛዙ ዘረኛ ቅስቀሳ እንዳይደናገሩና ከሕዝብ ጋር እንዲወግኑ መጣር አስፈላጊ ነው:: የፌዴራል ፖሊስ፤ ጦር ወዘተ ተብለው በመለስ የሚታዘዙት ደግሞ ብረታቸውን ወደ ሕዝብ ሳይሆን፥ ወደ አገዛዙ እንዲወድሩ መቀስቀስ በጣም ሚዛ ያለው ሥራ ነው::

ዛሬ የሕዝብ ፍላጎት፥ የቆሰለውን የመለስ አገዛዝ ማከም አይደለም:: የቆሰለን አውሬ አያያዝ ማወቅ ቢያሻም አክሞ ለማዳን መጣሩ፥ የሕዝብ ፍላጎትም ሆነ ዓላማ አይደለም:: የአገዛዙ አሸናፊነት ተቀብሎ የመለስ ቡድን በበላይነት በሚወራጭበት ፓርላማ ተብዬ በረት መርመስመስ የሕዝብን ድምፅ ማስከበር ተብሎ ሊወሰድ አይችልም:: የሚጠቅመው ለአገዛዙ ነው:: ጊዜ አግኝቶ፤ ካለፈው ተምሮና አፈናውን አጠናክሮ የሚወጣው ወያኔ ብቻ ይሆናል:: በሕዝብ ላይ ይበቀላል፤ የትግሉን መንፈስ ያዳክማል:: ዛሬ ሕዝብ ድምፁን ሰጥቶ ተቃዋሚ ኃይሎችን አሸናፊ አድርጓል:: ይህ ውሳኔና ምርጫ መከበር አለበት እንጂ ለሌባ አሳልፎ ሊሰጥ አይገባውም:: አገዛዙ ውድቀቱ መጥቶበታልና እንደ ቆሰለ አውሬ ቢያጓራ ቢደነፋ፤ ቢያስር -ቢገድል ፥ የሕዝብ የጋራ ትግል ጠንክሮ ከቀጠለ ከውድቀቱ አያመልጥም:: የኃይል ብዛትና ጭካኔ ከውድቀትና ሽንፈት ያዳነው ሥርዓት ወይም አገዛዝ የለም ማለት ማጋነን አይደለም:: ለዚህም ነው፥ ተማሪዎች ያሰሙት ታሪካዊ ጩኸት፥ በከተሞችና በገጠሩም ተስተጋብቶ የመለስ አገዛዝ ተወጥሮና ተዋክቦ ለሽንፈት መዳርግና መወገድ ያለበት:: በአገዛዙ ስር ያሉት የፖሊስና የጦር ኃይል አባላትም ተጠሪነታቸው፥ ለሀገረና ለሕዝብ እንጂ፥ ለተጠላ ቡድን አይደለም ብለው ለመለስ ቡድን አንታዘዝም እንዲሉ ይጠበቅባቸዋል:: ሕዝብ የመረጠው ኃይል ማን ይሁን ማን የሥልጣን ባለቤት መሆን አለበት--ወሳኙ ሕዝብ ነውና:: የመለስ ቡድን በሕዝብ ወግድ ተብሏል--በሥልጣን ከቶም

***ሊቀጥል አይችልም:: ሙከራውንም በትግል ማከሸፍ ግዴታችን ነው:: ኢሕአፓ በሀገር ቤት ያሉት አባላቱ ሁሉ የህቡዕ ትግላችውን መመሪያ ሳይዘነጉ የሕዝቡን ትግል እንዲያፋፍሙና አስፈላጊውንም መስዋዕትነት እንዲከፍሉ የጠራው ይህ አስፈላጊ በመሆኑና የመለስ ቡድንም በምለላ የሚወገድ አለመሆኑን በማወቁ ነው::***

***የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ቆራጥና ታሪክ አዳሽ ትግል መስፋፋት አለበት:: ፍትሀዊና ወቅታዊ ነው ትግላቸው:: በሥራ ማቆም አድማና በሌላም የሕዝብ አመፅ መደገፍ አለበት:: የድርጅቶችም ሚና ይህንን ትግል ማቀናጀትና ማፋፋም እንጂ ማቀዝቀዝ ሊሆን አይችልም:: የመለስን ቡድን ነብር ማለት ባይቃጣንም የነበርን ጭራ አይዙ ከያዙም አይለቁ ማለቱ ግን ቦታው ነው:: ትግሉ ተጀምሯል--ሸብረክ ማለት ማፈግፈግ አይቻልም ወይም ለከፋ ጉዳት ይዳርጋል:: መልፈስፈሰም ያስመታል፤ያስተዛዝባል:: ተማሪዎችም ሕዝብም የሚጠይቁት ጉምን አሰጨብጡን የሚል ሳይሆን÷ የምርጫ ድምፃችን መብታችን ይከበር የሚል ነው:: ይህ ድርደር አያሻውም:: በግማሽ መብታችንን ውሰድ፤በግማች ተውልን ብሎም ነገር ሊኖር አይችልም:: በግማሽ ልብ ትግል ለሀገር አይፈይድም:: ሕዝብ በየምርጫ ጣቢያው እያደረ÷ ድምፁን ያስቆጠረው የተወሰኑ የተቃዋሚ ድርጀቶች በወያኔ ፓርላማ ገብተው ወንበር እንዲይዙ፥ ሳይሆን÷ የመለስ አገዛዝ እንዲወገድ ነው:: ይህን መሳት ደግሞ የሀገራችንን ሁኔታ መሳትና በአልባሌ ጥቅም መታወር ወይም አገዛዙ መፍራት ይሆናል:: በሥልጣን ያለውን ቡድን በደፈናው ሞቷል ብለን ባንቃጣም÷ ለደቂቃ ግን የምንፈራው አይደለንም:: ለዚህም ነው ኢሕአፓ ለተማሪዎች በርቱ ቀጥሉ እያለ ሕዝብንም በትግል ተማሪዎችን እንዲያጅብ ጥሪ የሚያስተላልፈው:: ወቅቱ የሚፈግፈጊያ ሳይሆን÷ ወደፊት ጠንክሮ የመግፊያና ገዢውን ቡድን የማስወገጂያ ነው:: ትግሉ መስዋዕትን ጠያቂ መሆኑን ደግሞ በወያኔ አገዛዝ÷ የሞት ሲጋት የባጀው ሕዝብ የሚያጣው አይደለም::***

***መፈክራችን በቃን እምቢ አንገዛም ይሁን!***
***ትግላችን የጋራና ግቡን ሳይመታ የማይቆም ይሁን!***
***በሕዝቡ ድል አድራጊነት እምነታችን የፀና ይሁን!***
***የመለስ መንጋ በትግላችን ይቸነፋል!!***